ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መሄጃ ኣንድ መንገድ ብቻ ነው ። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም (ዮሐ 14:6) ። መዳንም በሌላ በማንም የለም ፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና (ሐዋ.ሥራ 4:12) ።

## የመንግሥተ ሰማያትን መንገድ እንዴት መጀመር ይቻላል ?

1. ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ : (ማር 1:15) ።
2. ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ና ። በጸሎት ከነኃጢኣትጥ ና እና ይቅርም እንዲልህ ለምን ። እርሱ እንዲህ ብሎሃል :- ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም (ዮሐ 6:37) ። እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ፥ ወደ እኔ ኑ ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ (ማቴ 11:28) ።
3. ከኃጢኣት ለመውጣት በክርስቶስ ብቻ እመን ። የልጁም የኢ.ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል (1ኛ ዮሐ1:7) ።
4. ኣዲስ ሕይወትና የዘለዓለም ሕይወት ይሰጥሃል ። ክርስቶስ እንዲህ ይላል :- ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም (ዮሐንስ 5 : 24) ። ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ፤ አሮጌው ነገር አልፎአል ፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል (2ኛ ቆሮንቶስ 5:17) ።
5. ሰላም በልብህ ይኖርሃል ። እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢ.ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ (ሮሜ 5:1) ። እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ (1ኛ ዮሐ 5:11-13) ።

## በኣዲስ ሕይወት መኖር እንዴት እንደሚቻል

1. መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉጊዜ ኣንብብ ። ለመንገዳችን ብርሃን ከመሆኑም ሌላ ለነፍሳችንም ምግብ ነው ። ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ ፥ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ (1ኛ ጴጥሮስ 2:2) ።
ቃሉን ስታነብ እግዚኣብሔር በመንፈሱ እንዲያስተምርህና እንዲመራህ ጸልይ ።
2. ሁሉግዜ በጸሎት ወደ እግዚኣብሔር ቅለብ ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጸልይ ። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢ.ኢየሱስ ይጠብቃል (ፊልጲ 4:6-7) ።
3. ለሌሎች ስለ ክርስቶስ መስክር ። ወደ ቤትህ በቤተሰዎችህ ዘንድ ሄደህ ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ እንዴትስ እንደ ማረህ አውራላቸው አለው (ማር 5:19) ።
4. በፈተናህ ጊዜ ጌታን ጥራው ። እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና (ዕብራውያን 2:18) ።
5. ኃጢኣትን ብትሠራ ወዲያውኑ ሄደህ ለጌታ ተናዘዝ ። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው (1ኛ ዮሐ 1:9) ።
6. በክርስቶስ ኢየሱስ ከወገኖች ጋር ኅብረት ይኑርህ ። እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት (ዮሐንስ 15:12) ።
7. ሁሉግዜ ጌታን ታዘዝ ። የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል (ዮሐ 14:23) ።
8. ክርስቶስ ካንተጋር ስለሆነ ኣትፍራ ። አልለቅህም ከቶም አልተውህም (ዕብራውያን 13:5) ።
9. ሕይወጥ ሙሉ በሙሉ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጥ ። እርሱ እንደ ኣሳቡና እና ፍቃዱ ይምራህ ። እንዲህ ካደረግህ እውነተኛ ደስታን ታገኛለህ ።





Distribution of Christian Literature 7.2017
Bernstrasse 73, CH-3613 Steffisburg, Switzerland
www.dclit.net / info@dclit.net Amharic



# ሁለት መንገዶች

## መንገድ መምረጥ

ሄደን ወደማናውቅበት ኣገር ለመ ሄድ ስናስብ የትኛው መንገደ እንደሚ ሻል እንመርጣለን ። ዓይኖቻችን ኣቅንተን በርቀት እንመለከታለን ። የጀመርነው መንገድ የተሳሳተ ከሆነ እንመለሳለን ትክክለኛውንም መርጠን ጉዞ እንጀምራለን ። መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊ ጉዞን ተያይዘናል ። በየዕለቱ እኔና እናንተ ብዙ ከመሄዳችንም የተነሣ ወደማንመለስበትም ቦታ እንደርሳለን ። የትእንደምትሄድ ታውቃለህ ?

## መሪ መጽሐፋችን

እግዚኣብሔር በፍቅሩና በርኅራኄው መሪ መጽሐፍ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶናል ። በዚህም ደግሞ በግልጽ እንዴት ወደ ገነት መድረስ እንደምንችል መንገዱን መርቶናል ። የዚህም ትራክት ጥቅስ የተወሰደው ከዚሁ መጽሐፍ ነው ። ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው: (መዝ 119:105) ።

## ሰፊው መንገድ

በዚህ መንገድ ላይ እጅግ በጣም ቡዙ ሰዎች ይገኛሉ ። በጠበበው ደጅ ግቡ : ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ : መንገዱም ትልቅ ነውና : ወደ እርሱም የሚገቡ ቡዙዎች ናቸው : (ማቴዎስ 7:13) ።

ቡዙዎቹ በዚህ መንገድ ላይ የሚጓዙት ዓይናቸው ታውሮኣል ። በጥፋት መንገድ ስለ መሄዳቸው ኣያውቁም ወይም ግዴላቸውም ። ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ ኣለች : ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው (ምሳ14:12) ። ለእነርሱም የእግዚኣብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ ዓለም ኣምላክ የማያምኑትን ኣሳብ ኣሳወረ (2ኛ ቆሮ4፥4) ።

## ሸክሞች

በዚህ መንገድ ላይ ያሉ ሰዎች በኃጢኣት ታስረዋል ። ሁሉ ኃጢኣትን ሠርተዋልና የእግዚኣብሔር ክብር ጐድሎኣቸዋል (ሮማ 3:23) ። ኣንድም ኃጢኣት ከእግዚኣብሔር ፊት መደበቅ ኣንችልም ። ሰው ፊትን ያያል : እግዚኣብሔር ግን ልብን ያያል (1ኛ ሳሙ፥ 16፥7) ። ሸክሙ በሰንሰለት ተጠፍሮባቸዋል ። እኔ እና እናንተ በራሳችን ኣቅም ከኣንዲት ኃጢኣት እንኳ ነፃ መውጣታ ኣንችልም ። የኃጢኣት ደምወዝ ሞት ነውና (ሮሜ 6፥23) ።

## መብረቅ

በዚህ ሥዕል ላይ የተመለከተው መብረቅ የእግዚኣብሔር ፍርድ ነው የሚያመለክተው ። ለሰዎችም ኣንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደተመደበባቸው (ዕብ 9፥27) ። ታላቅና ነጪ ዙፋንን በእሱም ላይ የተቀመጠውን ኣየሁ ፥ ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሸሹ ስፍራም ኣልተገኘላቸውም ። ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው ኣየሁ : መጻሕፍትም ተከፈቱ : ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሃፍ ነው ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈተ ። ... በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ (ራእይ 20:11.12.15) ።

## እሳት

እግዚኣብሄር ጽድቅና እውነት እንደሆነ ሁሉ የኃጢኣት ቅጣት መኖር ግዴታ ነው ። የእግዚኣብሄር ቃል እንደሚገልጽልን እግዚኣብሄር ለማያምኑት የተዘጋጀ የዘለዓለም ቅጣት ገሃነም እሳት እንዳለ ይነግረናል ። መጽሓፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል :- መጨረሻቸው ጥፋት ነው : ሆዳቸው ኣምላካቸው ነው : ክብራቸው በነውራቸው ነው : ኣሳባቸው ምድራዊ ነው (ፊሊ. 3:19) ።

እግዚኣብሄር ግን የፍቅርም ኣምላክ ነው ። ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል (2ኛ ጴጥ 3:9) ። በዚህ ታላቅ ፍቅሩን ቸርነቱ ለሁሉ የሚሆን የማምለጫ መንገድ (ዘዴ) በእውነት ለሚፈልጉት ኣዘጋጅቶኣል ። የሕይወትን መንገድ ትፈልጋለህ ?

## ኣዳኙ :- የሕይወት መንገድ

ከኃጢኣትና ከቅጣቱ ራሳቸንን ነፃ ማውጣት ስለማንችል እግዚኣብሄር ኣንድ ኣዳኝ ሰጠን ። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና (ዮሐ 3:16) ። ኣብ ኣንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከልን ። ከሰማይ መጥቶ በዚህች ምድር እንደ ሰው ሆኖ ኖረ ። ኃጢኣት ግን ኣልሠራም ። የታመመን እየፈወሰ : ሽባን ኣያዳነ : መናፍስትን እያስወጣ : ተጸጽተው ኃጢኣታቸውን ለሚናዘዙ ይቅር እያለ እና ስለ እግዚኣብሔር ለሰዎች እያስተማረ ኖረ ። ትልቁ ዓላማው ግን ሥጋን ለብሶ ስለ ኣኛ ለመሞት መምጣቱ ነው ። መለኮቱን እና የተቀደሰ ሕይወቱን ሊሰጠን : ስለ ኃጢኣታችን ይቅርታ ቅዱስ ደሙን ሊያፈስልን መጣ ። ኃጢኣተኞች ወስደው ሰውነቱ እስኪሰነጣጠቅ ድረስ ጀርባውን እንዲገርፉት : ካላቱም በደም እስኪሸፈን የእሾኽም ኣክሊል ሠርተው በራሱ ላይ ኣንዲደፉበት : ከዚህም ኣልፎ እጁና እግሩን ሸንክረው በመስቀል ላይ እንዲሰቅሉት ፈቀደ ። ታላቅ ሥቃይና ሕመም እስኪቀምስ ድረስ ተሰቀለ ። እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ : በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ (1ኛ ጴጥሮስ 2:24) ። እርሱም ለእኔና ላንተ ሞተ ።

## ትንሣኤው

ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተ በሦስተኛ ቀኑ ከሞት ተነሣ ። በምድርም ላይ በመንቀሳቀስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተነጋግሮኣል ። ከኣርባ ቀንም በኋላ ወደ ሰማይ በማረግ ከኣብ ቀኝ ተቀምጦኣል (ሮሜ 8:34) ። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ (ማቴዎስ 28 :18) ። ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል (ዕብራውያን 7:25) ።

## ገነት (መንግሥተ ሰማያት)

እግዚኣብሔር ከነሙሉ ክብሩ የሚኖርባት ኣገር ገነት (መንግሥተ ሰማያት) ናት ። ጌታ ኢየሱስ ዓንዲህ ብሎኣል :- ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ (ወ.ዮሐ 14:2-3) ።

እጅግ የሚደነቅቦታ ነው ። እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል ፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና (ራእይ 21:4) ። ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም ፥ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም ፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ (ራእይ 22:5) ።

የተቀደሰ ቦታ ነው ። ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር ፥ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም (ራእይ 21:27) ። ▶